የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ህብረቱ በአትላንታ ማብራሪያ ሰጠ

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከፍተኛ የአመራር አባላት የሆኑት አቶ አረጋዊ በርሄ ፤ ዶ/ር ስዩም ገላዬና የታወቁ የህግ ምሁር የሆኑት ዶ/ር አለምአንተ ገብረስላሴ በ07/29/2006 በአትላንታ ከተማ በመገኘት በአካባቢው ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል ፤ ፤

በዚህ ስብሰባ ወቅት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ፖለቲካዊ ራእይ ከግንቦቱ ምርጫ በፊትና በኋላ ምን እንደሚመስል መግለጫ ከመሰጠታቸውም በላይ ህብረቱ ያነሳቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት መሰረታዊ መሆናቸውን ህዝቡ እንዲገነዘብ ለማድረግ ችለዋል ፤ ፤

በሁለተኛ ደረጃ ሰፊ ማብራሪያ የተሰጠበት ጉዳይ በቅርቡ የተመሰረተው «ትብብር ለነጻነትና ዴሞክራሲ»ን በተመለከተ ሲሆን ይህን ድርጅት ለመመስረት የነበረው ሂደትና ከዚያም በኋላ በትብብሩ ፈጣሪዎች የቀረቡት ዶክመንቶች የህብረቱን የፖለቲካ ራእይ የሚያጨናግፉ የኢትዮጵያን ሉኣላዊነትና ዘላቂ አንድነት ሊያናጉ የሚችሉ ስምምነቶችን የያዘ በመሆኑ ህብረቱ የትብብሩ አካል ለመሆን አለመቻሉን ከተገለጸ በኋላ አሁንም እነዚህ ዶክመንቶች የሀገርን ሉኣላዊነትን ከአደጋ ላይ በማይጥል መልክ የሚቀየሩበት ሁኔታ ከተመቻቸ ህብረቱ ከሁሉም ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አስረድተዋል ፤ ፤

በዚህ ስብሰባ የተሳተፉት አንዳንድ ሰዎች የትብብሩ ሂደትና የተስማሙባቸው ዶክመንቶች ያላቸውን ችግር ከገለጹ በኋላ ቢሆንም ከውስጥ ሆናችሁ ለምን አትታገሉም የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርበው የነበረ ሲሆን የህብረቱ ተወካዮች በትብብሩ ስብሰባ ውስጥ በመሆን በዚህ መልክ ታግሎ ውጤት ለማግኘት የሚያሰችል ሁኔታ አለመኖሩን መረጃዎች በማጣቀስ ከማስረዳታቸውም በላይ በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚያገባቸው ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራትንም የሚያካትት ሰፊ መድረክ በመፍጠር ይህን አዝማሚያ መለወጥ ካልቻልን በጥቂት ቡድኖች

የድብቅ አጀንዳ ተጠልፈን ብሄራዊ አንድነታችንና መብታችን የማሰከበሩ ጉዳይ እጅግ አደጋ ላይ ይወድቃል በማለት አስረድተዋል ፤ ፤

በዚህ ስብሰባ ከቀረቡት ሌሎች ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ ድርጅቶች በተለይም ህብረቱና ቅንጅቱ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት ከህዝብ ፊት ያላቸውን አንድነቶችና ልዩነቶች ለምን አያቀርቡም የሚል ሲሆን ይህን በተመለከተ ህብረቱ ፈቃደኛ መሆኑን ሲያረጋግጡ ከቅንጅቱ በኩል ግን እን ደዚህ አይነቱን ውይይት ከህዝብ ፊት ከህብረቱ አመራሮች ጋር ለማድረግ የማይፈልጉ መሆናቸውን ሲገልጹ ባለፈው አመት አትላንታ ላይ በዚህ አመት ደግሞ ሎስ አንጀለስ በዚህ መልክ የተደረገውን ዝግጅት አንቀበልም በማለት ድርጅቶቹ በግል ብቻ ስብሰባ እንዲያደርጉ ማድረጋቸውን አ ብራርተዋል ፤ ፤

በዚህ ስብሰባ የተገኙት ኢትዮጵያን በተለይም ደግሞ የኡጋዴንና የአንዳንድ አካባቢዎች ተወላጆች በአንዳንድ አካባቢ የሚካሄዱት ጦርነቶች አንዳንድ ቡድናዊ ጥቅሞችን ለማሟላት የሚደረጉ ብቻ ናቸው ድርጅቶችም ህዝባዊ አጀንዳ የላቸውም ካሉ በኋላ የሀገራችን ችግር መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው በህዝብ መሰረታዊ ችግሮችና በሀገራዊ ጥቅም ላይ ያተኮረ ስምምነት ተደርጎ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚያስተባብር ትግል ሲደረግ ብቻ ነው ብለዋል ፤ ፤ በዚህም ሃሳብ በቤቱ ውስጥ ሙሉ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ከሁሉም በላይ የሀገር ሉኣላዊነትና የህዝብ መብት መከበር መቅደም አለበት በማለት ስብሰባው ተጠናቋል ፤ ፤

## በአትላንታ የህብረቱ ድጋፍ ኮሚቴ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132